# مقدمة وغلاف المنتقى من موسوعة الأحاديث النبوية

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በኾነው እጀምራለሁ

መቅድም

ምስጋና ባጠቃላይ ለአለማት ጌታ ለአሏህ የተገባ ነው። የአሏህ ውዳሴና ሰላም በነቢያችን ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው እንዲሁም እስከ እለተ ትንሳኤ ድረስ በተከተላቸው ላይ ሁሉ ይስፈን። በመቀጠል:

አንድ ሙስሊም ከቁርአን ቀጥሎ በማንበቡም፣ በመማሩም፣ በማስተንተኑ በኩልም፣ በመተግበሩ ረገድም ትልቁን ትኩረት ሊቸረው የሚገባው ጉዳይ ቢኖር የረሱል - ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም (የአሏህ ሶለዋትና ሰላም በሳቸው ላይ ይስፈንና) - ሱናቸውን ነው። ነቢዩ (ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም) የአሏህ ውዳሴና ሰላም በርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ ብለዋል:

«تركتُ فيكم أيُّها الناس، ما إنِ اعتصمتم به، فلن تضلُّوا أبدًا: كتاب الله، وسُنَّة نبيِّه»

«ሰዎች ሆይ! አጥብቃችሁ ብትይዙት መቼም የማትጠሙበት የሆነን ነገር በመካከላችሁ ትቼላችኋለሁ: ይኸውም የአሏህ ኪታብ እና የነቢዩ ሱና ነው።» ኢማም ማሊክ ዘግበውታል። የላቀው አሏህ እንዲህ ብሏል:

{وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانْتَهُوا}

{መልክተኛውም የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ።} [አል-

ሐሽር: 7] ለዛም ሲባል የኢስላማዊ ይዘቶች በቋንቋዎች አግልግሎት ማህበር እና፣ በረብዋ የዳዕዋና ኮሚኒቲ ግንዛቤ ማስጨበጥ ማህበር  ነቢያዊ ሓዲሦችን በኢንሳይክሎፒዲያ መልክ አጠናቅሮ በተለያዩ ቋንቋዎች የመተርጎም እቅድን ሰነቁ።

የላቀው አላህ አግርቶት ሙስሊሙ በዲኑም በዱኒያውም ጉዳይ የሚያስፈልገውን የሓዲሦች ክምችት አጠር ካለ ማብራርያ፣ ሀሳብና ጥቆማዎች እንዲሁም በውስጡ የያዛቸውን ፍሬ ሀሳቦች ከመግለፅ ጋር ተጠናቅሯል። ተከታዩን ስያሜ በያዘ መጽሃፍ ተዘጋጅቶ ወጥቷል: «ሙንተቃ (ከነቢያዊ ሓዲሦች ኢንሳይክሎፒዲያ የተውጣጣ ጥንቅር)» መላው አለም በይዘቱ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ እና የአላህ መልክተኛ ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም ሱና በየቋንቋቸው ሊደርሳቸው ዘንድ ስራው በዓለም ታላላቅ የቋንቋዎች በመተርጎም ላይ ነው።

አላህን ይህንኑ መልካም ስራ እንዲቀበለን፣ ስራውንም የተባረከና ለርሱ ተብሎ የተሰራ እንዲያደርገው፤ በዝግጅቱም፣ በትርጉሙም ይሁን በስርጭቱም ላይ የተሳተፈውን ሁሉ መልካም ምንዳ ይመነዳው ዘንድ እንማፀነዋለን።

የአሏህ ውዳሴና ሰላም በነቢያችን ሙሐመድ ላይ ይስፈን

አጠር ያለ ገለፃ

ነቢያዊ ሓዲሦች ከኢስላማዊ የድንጋጌ ምንጮች (ከቁርአን ቀጥሎ) ሁለተኛው ምንጭ ነው። የላቀው አሏህ እንዲህ ብሏል:

{وَمَا يَنْطِقُ عَنِ الْهَوَى (٣) إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْيٌ يُوحَى}

{ከልብ ወለድም አይናገርም፡፡} (3)

{እርሱ (ንግግሩ) የሚወርረድ ራእይ እንጅ ሌላ አይደለም፡፡} (4) [አን-ነጅም: 3 - 4]

ይህ የነቢያዊ የሓዲሦች ኢንሳይክሎፒዲያ ጥንቅር ጥቅል መልዕክት ያላቸው ለሙስሊሙ በዲኑም በዱኒያውም ጉዳይ የሚያስፈልገውን የሓዲሦች ክምችት አጠር ካለ ማብራርያ፣ ሀሳብና እንዲሁም በውስጡ የያዛቸውን ፍሬ ሀሳቦች ከመግለፅ ጋር የተዘጋጀ ነው። መላው አለም በትምህርቱ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ እና የረሱላቸው ሶለሏሁ ዓለይሂ ወሰለም ሱና በየቋንቋቸው ሊደርሳቸው ዘንድ ስራው በዓለም ታላላቅ ቋንቋች በመተርጎም ላይ ያለ የሓዲሦች ጥንቅር ነው።

# ማውጫ

No table of contents entries found

am375v1.0 - 04/09/2026